# ለጥሩ የስንዴ ምርት ትክክለኛ የንጥረ ነገሮች አጠቃቀም



## የፎስፈረስ ጥቅሞች

- ተክሎች ጤናማ ስሮችን እንዲያወጡ ይረዳቸዋል
- ተክሎች ፈጥነው እንዲያብቡ ያደርጋቸዋል
- ተክሎች በበቂ ሁኔታ እንዲዋለዱ ያግዛል
- ፈጣንና ወጥ የሆነ የሰብሎች መጎምራት እንዲኖር ያደርጋል
- የስንዴ ምርት በዘላቂነት እንዲጨምር ያደርጋል



# ፎስፎረስ - ስንዴ




የፎስፈረስ እጥረት ያለበት የስንዴ ቡቃያ ያረጀው የቅጠሉ ክፍል መልክ ወደ ሓምራዊነት ይቀየራል

## በፎስፎረስ እጥረት ምክንያት በተክሎች ላይ የሚታዩ ምልክቶች

- የተክሎች መጠን አነስተኛ መሆንና የስሮቻቸው አጭር መሆን
- በቅጠሎችና ግንድ ላይ ሃምራዊ ቀለም መታየት
- የቅጠል ጫፎች የተቃጠሉ መስለው መታየት
- የሰብሎች የመዋለድ መጠን መቀነስ
- የዘገየና ያልተስተካከለ የሰብል መጎምራት



የፎስፎረስ እጥረት ያጋጠመው ሰብል የቀነጨረና የተዳከመ ዕድገት ያሳያል



የፎስፎረስ እጥረት ያጋጠመው የሰብል ቅጠል መልኩ ቢጫ ብርቱካናማ ወይም ሃምራዊ ብርቱካናማ የሚመስል ይሆናል

### ትክክለኛ ምንጭ

የፎስፎረስ ምንጭ ተብለው የሚታወቁ የማዳበሪያ አይነቶች ዳፕና ኤንፒኤስ ሲሁኑ ለአብነት እንደ 19፡38፡0 +7(ሰልፈር) እና 19፡38፡0+7 (ሰልፈር) ሲደመር 2.2(ዚንክ) ያሉ የዳፕ እና ኤን ፒ ኤስ ማዳበሪያዎች የሚመከሩ የማዳበሪያ አይነቶች ናቸው፡፡

### ትክክለኛ መጠን

እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ቢወሰንም፤ ትክክለኛው የፎስፎረስ መጠን ከ40-50 ኪ.ግ በሄክታር ነው፡፡ ለስንዴ ማሳችን በምንጠቀመው ማዳበሪያ ውስጥ ያለውን የፎስፎረስ መጠን ፤ ባለን የእርሻ ቦታ ስፋት፤ የአፈር አይነት እና ለማግኘት በታቀደው ምርት መሰረት ለመወሰን በአቅራቢያ የሚገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ማማከር አስፈላጊ ነው፡፡

4R Solution

https://4rsolution.org

### ትክክለኛ ጊዜ

ፎስፎረስን የያዙ የማዳበሪያ ዓይነቶችን በዘር ወቅት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ የተሻለ ምርት ለማግኘትም ከፎስፎረስ ጋር በአንድነት ጥቅም ላይ የሚውሉ እንደ ናይትሮጂን ያሉ ሌሎች ንጥረ ነገሮች በትክክለኛው መጠናቸው መገኘታቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

### ትክክለኛ ቦታ

በዘር ወቅት ማዳበሪያን ወጥ በሆነ መልኩ በጤፍ ማሳ ላይ መበተንና አፈር በስሱ ማልበስ ያስፈልጋል

In partnership with Canada · Co-operative Development Foundation of Canada (since 1947) · Fertilizer Canada / Fertilisants Canada · Plant Nutrition Canada · CFPN Center for Fertilization and Plant Nutrition · International Potash Institute (since 1952) · ewnra · APNI African Plant Nutrition Institute